በተጨማሪም ጨቅላው ከተወለደ በኃላ በእናትየው በግፍ ታፍኖ ህይወቱ የሚያልፍበት ሁኔታ አለ፡፡

እባክሽን ልጅሽን አትግደይ

ይህንን ችግር ለመቅረፍና ከከንፈርና ላንቃ ክፍተት ጋር የሚኖሩ ህፃናት ልጆች ያሏቸውን ወላጆች ለመደገፍ የሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይገኛሉ፡፡

እባኮዎትን ባለሙያዎችን ያማክሩ፡፡

ከልዩነት ጋር የተወለዱ ህፃናት በጤንነት እንዲያድጉ እንመኛለን፡፡



Established in 1992

ዶ/ር ሳምሶን ንጉሴ
(አ.አ.ዩ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጥርስ ህክምና ት/ክፍል)
ኢሜል፡lambadina4@yahoo.com
ስልክ፡ +251-922-566814

# ለወላጆች በተፈጥሮ ስለሚከሰት የከንፈርና ላንቃ ክፍተት የተዘጋጀ አጭር መልዕክት

ከፓናሶኒክ NPO የአፍሪካ ድጋፍ ፈንድ
በተገኘ ገንዘብ በጃፓን የከንፈርና የላንቃ
ክፍተት ፋውንዴሽን የተዘጋ
እኤአ 2017 ዓም

የጃፓን የከንፈርና ላንቃ ክፍተት
ፋውንዴሽን ከፓናሶኒክ ኩባንያ ጋር
በመተባበር የተዘጋጀ

2017

የከንፈርና ላንቃ ክፍተት በተፈጥሮ ከውልደት በፊት የሚከሰት ችግር ነው፡፡

ይህ ሁኔታ በማንኛውም ህፃን ላይ ሊከሰት ይችላል፡፡

የከንፈርና ላንቃ ክፍተት ሁለት ሰዓት በማይሞላ ቀዶ ህክምና ይስተካከላል፡፡




እባክዎትን ባለሙያዎችን ያማክሩ፡፡

በተፈጥሮ በሚከሰት የከንፈርና ላንቃ ክፍተት ምክንያት ቦታቸውን ሳይጠብቁ የበቀሉ ጥርሶች በህክምና ይድናሉ፡፡



በአግባቡ ያልበቀሉ ጥርሶችን ለማስተካከል የሚሰጠው ህክምና ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ ክትትሎን አያቋርጡ፡፡

በተፈጥሮ ከሚከሰት የከንፈርና ላንቃ ክፍተት ጋር ተያይዞ በሚመጣ የንግግር ክህሎት መዘግየት ችግር ህፃናት ይጨነቃሉ፡፡

ለሁሉም ህሙማን በትክክለኛ ባለሙያ የንግግር ምርመራ ቢደረግላቸው በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

የተሟላ የንግግር ክህሎት ምርመራ ማድረግ የሚቻለው ህጻኑ 4 ዓመት ሲሞላው ብቻ ነው፡፡

በተፈጥሮ የሚከሰት የከንፈርና ላንቃ ክፍተት ያለባቸው ህፃናት ለጆሮ ህመም የተጋለጡ ናቸው፡፡




የህፃኑ የማዳመጥ አቅም በየጊዜው እንዲጨምር ታማሚው መደበኛ የሆነ የባለሙያ (ኦቶላሪንጎሎጂስት) ክትትል እንዲያደርግ ይመከራል፡፡

ከቅድመ ወሊድ በፊት በሚደረግ ምርመራ ምክኒያት ሙሉ በሙሉ ሊድን በሚችል የተፈጥሮ በሽታ የተጠቁ ጨቅላ ህፃናት ውርጃ ይፈፀምባቸዋል፡፡

እባክሽን ስላውርጃ ፈፅሞ አታስቢ፡፡

